# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**<u>አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን አባላት ስብሰባ</u>**

አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን አባላት ስብሰባ በ4/28/19 ከመደበኛው የአምልኮ ፕሮግራም በኋላ ይኖረናል። በዚህ ስብሰባ በ2018 የተፈጸሙ አንዳንድ ክንውኖችና የፍይናንስ ሁኔታን እንመለከተታለን። እደዚሁም አጠቃላይ የውይይት ጊዜ ይኖረናል። አባላት ሁሉ በዚህ ፕሮግራም ላይ እንድንገኝ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች።

**<u>በቤተ ክርቲያን የተዘጋጀ ታላቅ ሪትሪት</u>**

**ቀን፡ 7/4 - 7/6/2019**
**ስልክ፡** (920) 294-3323 Booking ID number= 14589 or Yemsrach
ያልተመዘገባችሁ ተመዝገቡ። በዚህ ፕሮግራም ፓስተር አሳየኸኝ ያገለግለናል።




| | | |
|---|---|---|
| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም።"
(ማቴ. 28:6)

| | |
|---|---|
| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m. |
| **April 21, 2019** | **ሚያዚያ 13፤ 2011 ዓ.ም.** |

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት ................ | ወንድም ረድኤቱ ግርማ ካሳ |
| አምልኮ...................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| የጥምቀት ስነ-ስረአት....... | ወንድም ብርሃኑ አንበሴ |
| የልጆች ድራማና ዝማሬ...... | የልጆች አገልግሎት ክፍል |
| ፕሮግራም መሪ .......... | እህት ሰናይት ከበደ |
| ቃል ............. | ወንድም ብርሃኑ አንበሴ |
| ማጠቃለያ ................ | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

# "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል።"

(ዮሐ. 11:25)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ተነሥቶአል!

*"ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም።" (ሉቃ. 24:5)*

የክርስትናችን መሰረቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ስለተነሳ ነው ከማይጠፋ ዘር ሁለተኛ የተወለድነው እና የማያልፍ ርስት የተጠበቀልን። (1ጴጥ. 1:3-5) ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ስለተነሳ ነው የትንሳኤ ተስፋ ያለን። (1ቆሮ. 15:20) ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተነሳ ነው የሞትና የሲዖል ኃይል የተሻረው። (ሮሜ 6:9) ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ስለተነሳ ነው ዲቢሎስ ድል የተነሳው። (ቆላ. 2:15) እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተነሳ ነው መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድር የመጣውና አሁን ከኛ ጋር ያለው። (ሐዋ. 2:33) መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት የሓጢያትን ስርየት አገኘን፣ በትንሳኤው ደግሞ የክርስቶስን ሕይወት ተካፍለን የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል።

የክርስቶስ ትንሳኤ በብዙ የማይታበል ማስረጃ የተረጋገጠ ነው። በሐዋ. 1:3 ላይ እንደምናነበው ጌታ "በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ" ራሱን ለደቀ መዛሙርቱ አሳያቸው። በአማርኛችን "ብዙ ማስረጃ" ተብሎ የተተርጎመው ቃል የማስረጃን ብዛት ብቻ ሳይሆን የሚያሳየው የማስረጃውንም የማይታበል መሆን ጭምር ነው። ስለዚህም በKing James Version ይህ ቃል "he shewed himself alive after his passion by many infallible proofs" ይላል። ቃሉ የማስረጃውን ብዛት "many" በሚለው ቃል ሲገልጽ፤ የማስረጃውን አይታበሌነት ደግሞ "infallible" በሚለው ቃል ይገልጸዋል። "Infallible" ለሚለው ቃል "Webster's" የተሰኘው መዝገበ ቃላት እንዲህ የሚል ፍቺ ይሰጠዋል፡ "incapable of error (unerring); not liable to mislead, deceive, or disappoint (certain); incapable of error in defining doctrines touching faith or morals." እንግዲህ ዶክተር ሉቃስ በጥንቃቄ እንደጻፈልን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ በብዙ ሊታበል በማይችል ጽኑ ማስረጃ የተረጋገጠ ነው።

የክርስቶስ ትንሳኤ በመላዕክት ምስክርነት ተረጋግጧል። መላዕክቱ ህያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋላችሁ በማለት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። (ሉቃ. 24:5) የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ በአይን ምስክሮች ተረጋግጧል። ጴጥሮስ በበዓለ-ሃምሳ ቀን ስብከቱ በአጽንዖት የመሰከረው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን መነሳቱን ነው። ለተሰበሰቡት "ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው <u>ለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን</u>" በማለት የአይን እማኝነቱን ሰጥቷል። (ሐዋ. 2፡ 32) በተጨማሪም አያሌ የአይን ምስክሮች ከሞት የተነሳውን ኢየሱስን እንዳዩት ሐዋሪያው ጳውሎስ ጽፎልናል። ("መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፥ ለኬፋም ታየ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ፤ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል። 1ቆሮ. 15፡ 4-8) የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ በታሪክም ተረጋግጧል። ለዚህም ነው ብዙዎች ሕይወታቸውን እስኪሰውለት ድረስ የተከተሉት።